# አገር እንዴት ሰነበተች ቁጥር 26

ነሐሴ 8 ቀን 2014 ዓም (14-08-2022)

የኢትዮጵያ አንድነት ራዲዮ የስነጽሑፍ ክፍል እያጠናቀረ በሚያቀርበው ሳምንታዊ አምዱ በዛሬው ቀንብሩ፣አዲስ አበባ አትገቡም ተብለው በመንገድ ላይ ስለታገቱት የአማራ ተወላጆች፣አዲስ አበባን የመዋጥ የኦሕዴድ /ኦነግ ድፍረት የተሞላው ውሳኔ ፣ባልተጠበቀው የባልደራስ ለእውነተኛ ዴሞክራሲ ፓርቲ ውስጥ ስለተከሰተው አሳዛኝ ሁኔታ ፣ በጉራጌ ማህበረሰብ ተወላጆች የክልል መሆን ጥያቄና በአባይ ግድብ ዙሪያ የተከሰቱትን የሚተነትን ይሆናል።

ባለፈው ሳምንት ቅንብራችን ካካተትናቸው እርእሶች አንዱ የነበረው ከወሎና ከጎጃም በኩል ወደ አዲስ አበባ ለመግባት በብዙ አውቶብሶችና የግል መኪናዎች የተንቀሳቀሱ ዜጎች አዲስ አበባ ለመግባት የአርባ ኪሎ ሜትር እርቀት ላይ ከሚገኘው ሰንዳፋና ከዛም ቀረብ ብሎ ካለው ሸኖ ከተባለው አነስተኛ ከተማ እንደደረሱ በኦሮሚያ ፖሊስ ታግደው ወደመጡበት እንዲመለሱ መደረጋቸውን ጠቆም አድርገን ነበር።እነዚህ በአማራነት ተፈርጀው ሳይፈቅዱና ሳይፈልጉት የጎሳ ማንነት መታወቂያ የያዙት ኢትዮጵያውያን ወደመጣችሁበት ተመለሱ ተብለው በአማራው ክልል የሰሜን ሸዋ ከተማ በሆነችው ደብረብርሃን ውስጥ በችግር ላይ መሆናቸውን ገልጸን ነበር።ይህ ችግር እስከዛሬም ድረስ ያልተፈታ ሲሆን መንግሥት ተብዬውም አካል ችግሩን ለመፍታት የወሰደው እርምጃ የለም።ይባስ ብሎ እርምጃው አዲስ አበባ ለመግባት የሞከሩትን የወያኔ ተላላኪዎችና አሸባሪዎችን ለመቆጣጠር ነው ሲል የወንጀሉን ትክክለኛነትና ተገቢነት ለማስረዳት ሞክሯል።

በዚህ ጉዞ ላይ የነበሩ ለሕክምና የሚሄዱ በሽተኞች፣ሕጻናትና አዛውንቶች፣እመጫቶችና ነፍሰጡሮች ለስቃይ ተዳርገዋል።ወንጀሉን ከፈጸመውና ካስፈጸመው የኦሮሙማው ክልል ባለሥልጣኖች ቀርቶ የዚያው ምርኩዝ ሆኖ በምንደኛነት የሚያገለግለው ብአዴን የተባለውም አሽከር ድርጅት በስሙ ለሚነግድበት ሕዝብ እንኳንስ ሊከራከርና መብቱን ሊያስጠብቅለት ቀርቶ ሰብአዊና ዜጋዊ መብታቸው እንዲከበር ፣አለያም ለገጠማቸው ችግር የሚሆን እለታዊ ድጋፍ ሲያቀርብ አይታይም።የአለቃውን የኦሕዴድን ጩኸት እዬጮኸ ንጹሃንን በመወንጀሉ ተግባር ላይ ተሰማርቷል።የአረመኔዎቹ ድርጊት ከማገድም ባለፈ መደብደብና ማንገላታት ከዚያም ባለፈ ተጓዦቹ ያላቸውን ገንዘብ የመዝረፍ እርምጃዎችን ያካተተ ሆኗል።ለመግባት ገንዘብ ካስከፈሉ በኋላ ለቀጣዩ ኬላ በማስረከብ ለተመሳሳይ መከራ የተዳረጉም ብዙዎች ናቸው።

ይህ አድራጎት የአውሮፓ አገሮች መንግሥታት ከተለያዩ አገሮች በተለይም ከአፍሪካ ስደተኞች ወደ አገራቸው እንዳይገቡ ከሚያደርጉት የመከላከል እርምጃ ቢብስ እንጂ ያነሰ አይደለም።በአውሮፓ ስደተኞች ሲታገዱ ከባሕር ላይ ሕይወታቸውን አትርፎ ወደ ቅርብ የወደብ መሬት የሚወስዱ ቀና ልብ ያላቸው ፈረንጆች በመኖራቸው ከሞት የተረፉ ብዙዎች ናቸው።ለዚህ ሳይበቁ የሞቱትም ቁጥራቸው ቀላል አይደለም።ከሞት የተረፉት ሌላው ቢቀር ወደመጡበት አካባቢ ይመልሷቸዋል እንጂ ውሃ ይብላህ አልተባሉም።በኢትዮጵያ ግን ኢትዮጵያዊው በገዛ ሃገሩ ዋና ከተማ እንዳይገባ ሲደረግና ለመከራ ሲጋለጥ ከተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶችም ሆነ ከሕዝቡ በኩል የደረሰላቸው የለም።ወደራሱ ከተማ መግባት ወንጀል ሆኖበት ወንጀለኞች በሚቆጣጠሩት መንግሥት የመከራ ሰለባ ሆኗል።ይህ አዲስ አበባን ከአማራው አጽድቶ ለመዋጥ ከተነደፈው የከተማዋን ነዋሪ የስብጥሩን መጠን ከመቀነስና ከማጨናገፍ እስትራቴጂ የመነጨ እኩይ ተግባር ነው።

በአዲስ አበባ የሚኖረው የአማራው ተወላጅ ለሌሎቹ ወገኖቹ መድረስ ያቃተው ብቻም ሳይሆን ተወልዶ ያደገባትና የሚኖርባት የአዲስ አበባ ከተማ በኦሮሙማው አገር ሰልቃጮች እንደ ዳቦ እዬቆራረሱ መሬቷን ሲቀራመቱ ለምን ብሎ ታግሎ ለማስቆም ቀርቶ ለመቃወምም ሞራሉ የፈሰሰ ሆኗል። ሰሞኑን የአዲስ አበባ ከተማ አካል የነበሩትን ክፍለ-ከተማና ወረዳዎች የኦሮሞ ክልል ናቸው በማለት ኦሕዴድና እንደራሴው የከተማዋ አስተዳደር በመስማማት እብሪት የተሞላበት የመሬት ዘረፋ ተካሂዷል።ይህ ነገ በእቅዳቸው መሠረት ከከተማዋ እዬለቀሙ በነቂስ ለሚያባርሩት ኦሮሞ ላልሆነው ኢትዮጵያዊ የማንቂያ ደወልና አሌ የማይባል አመላካች ነው።ሕዝቡ ግን በተደጋጋሚ እያዬም እዬሰማም ከእንቅልፉ ሊነቃ አልቻለም።አመላካቾች ቢኖሩም፣በእኛም ሆነ በሌሎቹ ተደጋግሞ ቢነገረውም ከሰፈረበት አዚምና ከተጫነው የፍርሃት ድባብ ሊላቀቅና ለመብትና ለሕይወቱ መትረፍ ሊታገል አልቻለም።ነጋዴውን በግብርና በቤት ኪራይ ጫና ፣ነዋሪውን በኑሮ ውድነት፣በሰላም ማጣት፣ በሥራ ዕድልና ፣የመኖሪያ ቦታና ቤት በመንፈግ ተመርሮ እንዲወጣ የማድረግ ስልቱም በሰፊው ቀጥሏል።ከተማዋን ለማያውቋትና ለማታውቃቸው የገኙው የኦሮሙማ ጎሳ ተወላጆች አሳልፎ በመስጠት ድፍረቱን ያሳዬ ሲሆን የጥቃቱ ሰለባ የሆነው የሌላው ጎሳ ተወላጅ የከተማዋ ነዋሪ ከገቢው ቆጥቦ የከፈለበትን የመኖሪያ ቤት መብቱን ተነጥቆ መክፈል ቀርቶ ከተማዋን ለማያውቁ ለዘረፋ ተመልምለው ለመጡ የኦሕዴድ/ኦነግ ደጋፊዎች ማስረከቡ በዬትኛውም የሕግ መስፈርት የማይደገፍ የሌቦችና የዘራፊዎች ድርጊት ነው። የጥቃቱ ሰለባ የሆነው የከተማዋ ነዋሪ ለብቻው ከማጉረምረም በስተቀር ተደራጅቶ ሲታገል አይታይም።መታገል ቀርቶ ለሚታገሉለት ደጀን አልሆነም።ይባስ ብሎም አማራውን የሚያስጠቁት በጥቅም የተገዙ ህሊና ቢስ የሆኑ የራሱ ጎሳ ተወላጆች ናቸው።በእነዚህ ከሃዲያን ላይ እንኳን እርምጃ ሊወስድና ፊት ሊነሳቸው አልደፈረም።

ጠላትማ ምን ጊዜም ጠላት ነው፣

አስቀድሞ መምታት ባንዳ አድርባዩን ነው።

የሚለው የአርበኞች አባቶቻችን ምክር የተረሳ ይመስላል።ለዚያም ነው የአድርባዩና የከሃዲው ቁጥር እያደር እዬጨመረ የሄደውና አድርባይነት፣መክዳት፣መዝረፍና መስረቅ የሚኮሩበትና የሚሞካሹበት መተዳደሪያ ሙያ የሆነው።

በመለመንና በመለማመጥ የሚተርፍ እዬመሰለው በጉቦ ገንዘቡን ይበትናል።መብቱንም ሃብቱንም አስረክቦ ባዶ እጁን ለመቅረት የመረጠ ይመስላል።ይህም አንዱ የኦሮሙማው ቡድን ስትራቴጂ ነው። በቀጣዩ ተጠርዞ መውጣቱን አውቆ መፍትሔ ካልፈለገለት የሚቀርለት አይሆንም።መፍትሔውም ተባብሮ ይህንን ጸረ ኢትዮጵያና ጸረ ኢትዮጵያዊ የሆነ ስርዓትና ጎሰኛ ቡድን ማሶገድ ብቻ ነው።

በጣም የሚገርመውና የሚያስቀው ቀልድ መሳይ መቀደድ ደግሞ የኦሮሙማው ቡድን ርእሰብሔር ነኝ ባዩ ሽመልስ አብዲሳ በእናቴ አማራ ነኝ፣እናቴ የጎጃም አማራ ነች፣አባቴ የሰሜን ሸዋ ኦሮሞ ነው።እኔን የአማራ ጠላት አድርገው በጭፍጨፋ ይወነጅሉኛል፤እንዴት የእናቴን ጎሳ እጠላለሁ? ሲል በአንድ የቃለመጠይቅ መድረክ ላይ መናገሩ ተገልጿል።አብይም እናቴ አማራ ነች ይላል፣ጁዋርም እናቴ አማራ ፣አጎቶቼም ቄስና ደብተራዎች ናቸው ይላል፤ግን ሁሉም አማራውንና የኦርቶዶክስ እምነትን መደበኛ ጠላት በማድረግ ጭፍጨፋ እንዲካሄድበት የቀሰቀሱና የመሩ ናቸው። ኦሮሞ መጀመሪያ!(Oromo First) በማለት ሁሉም ነገር የኦሮሞ፣ኢትዮጵያ በምንፈልጋት መልክ ካልያዝናትና ካልተቆጣጠርናት ትፈራርስ ከሚለው አቋማቸው የእናቶቻቸው እትብት ሊገታቸው አልቻለም።ዋናው ነገር የአማራ ተወላጅ መሆኑ ሳይሆን በሰብአዊነት ለአማራው ብሎም ለኢትዮጵያ መቆሙ ነው።ቅልጥ ያለው መንዜም ሆነ ጎንደሬ ቢሆን ለኢትዮጵያና ለአማራው በአጠቃላይ ለሰው ልጆች ካልቆመ የእናቱ ወይም

የአባቱ የዚህ ወይም የዚያ ጎሳ ተወላጅ መሆኑ ከሚሰራው ወንጀል ነጻ አያደርገውም።ሽመልስም ሆነ ጁዋር፣አብይም ሆነ ዳውድ ኢብሳ፣ሌሎቹም አክራሪ ኦሮሞዎች የሚፈረጁት በሠሩት ሥራ እንጂ በእናት በአባቶቻቸው ማንነትና ስነምግባር አይደለም።መሆንም የለበትም።ሌላው የዚሁ የሽመልስ ጉድ ስለአባቱ የደርግ ሹመኛ መሆንና በአምቦ ከንቲባነት ፣ከመንግሥቱ ሃ/ማርያም ጋር የቅርበት የዓላማ ግንኙነት እንደነበራቸው የገለጸው ነው።ታዲያ ሳያስበው በአባቱ ከንቲባነት በአምቦ ከተማ በቀይሽብር ለተጨፈጨፉት ወጣቶች ተጠያቂ እንደሚሆኑ ዘንግቶታል።ብዙ ነገር ካባቱ እንደቀሰመ ሲገልጽ አሁን እሱ የሚፈጽመው የአማራው ጭፍጨፋ ጭካኔ ከዚያ መምጣቱን እዬተናገረ መሆኑን ያሰበው አይመስልም።በአሁኑ ጊዜ ይህንን ለማለት ምን አስገደደው የሚል ጥያቄ ቢኖረንም የአቦን ስለት የበላ በአቦ እለት ዋዜማ ሌሊት ሲለፈልፍ ወይም ሲቃዥ ያድራል! በሚለው ካላሰርነው በቀር እንተንትነው ብንል ቦታና ጊዜ አይበቃንም።የሰው ደም ያቃዠል፣ያቅበጠብጣል፣ያስቀባጥራል!!

ከአዲስ አበባ ሳንወጣ ስለአዲስ አበባና ነዋሪዋ መብትና ሰላማዊ ኑሮ ለመታገል የተቋቋመው ባልደራስ ለእውነተኛ ዴሞክራሲ የተባለው የፖለቲካ ድርጅት የጥቃቱ ሰለባ ከሆነ ውሎ አድሯል።ብዙ መስዋእትነትን የከፈሉ ጋዜጠኞች፣አገር ወዳድ ወጣቶች፣ምሑራን፣የሕግ ባለሙያዎች የተሰለፉበት ይህ ፓርቲ እንዳይንቀሳቀስ የተዘረጉበት መሰናክሎች ለማለፍ ብዙ የጣረና ውጣ ውረዶችን ያለፈ ድርጅት ነው። በሕዝብ ያለው ተቀባይነትና በመሪዎቹ አልበገሬነት የተረኛውን የኦሮሙማ ቡድን እንቅልፍ የነሳውና የፖለቲካ ሽብር የነዛበት ይህ ድርጅት ከጥቂት ሳምንታት ወዲህ ግን የመዳከም አዝማሚያ ታይቶበታል።ከመዳከምም ባለፈ የመሪው የአቶ እስክንድር ነጋ ድምጽ መጥፋቱና ዬት እንዳለ አለመታወቁ በፓርቲው አባላትና ደጋፊዎቹ ብቻ ሳይሆን ፓርቲውን ተስፋ ባደረጉት የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ብቻ ሳይሆን ለኢትዮጵያ አንድነት በሚታገሉት ዘንድ ትልቅ ስጋት ፈጥሮ ሰንብቷል።

ድርጅቱ ውስጥ ምን እንደተፈጠረ የታወቀ ባይሆንም ከቀናት በፊት በነሓሴ 4 ቀን 2014 በአቶ እስክንድር ነጋ በሃምሌ 16 ቀን 2014 ዓም በእጅ ተጽፎ ተላከ በተባለው ደብዳቤ ላይ አቶ እስክንድር ተረኛው መንግሥት በፈጠረው ተጽእኖና ችግር ምክንያት በፓርቲው ካለው የአመራርም ሆነ የአባልነት ቦታ ለመልቀቅ እንደተገደደ ግልጿል።እሱንም ተከትሎ በማግስቱ በነሓሴ 5 ቀን 2014 ዓም የፓርቲው የሕዝብ ግንኙነትና የሕግ ባለሞያ የሆነው ጋዜጠኛ ጌጥዬ ያለው በድርጅቱ ውስጥ በተሰጠው የአላፊነት ቦታም ሆነ በአባልነት እንደማይቀጥል ለፓርቲው ያለውን ቀና ምኞት በመግለጽ የመሪውን የአቶ እስክንድርን ፈለግ ተከትሎ ከድርጅቱ መልቀቁን በጻፈው ደብዳቤ ይፋ አድርጓል። ሁለቱም ዬትና በምን ሁኔታ ላይ እንዳሉ የሰጡት ፍንጭ የለም።ስለሁኔታው የድርጅቱ የውጭ ድጋፍ አስተባባሪ የሆነው ግለሰብ በኢትዮ360 ላይ ቀርቦ በሰጠው ማብራሪያ አቶ እስክንድር በመልካም ጤንነት ላይ መሆኑን ከመግለጽ በላይ ዬትና ምን እያደረገ መሆኑን እንደማያውቅ አስረድቷል።ይኸው ግለሰብ ጨምሮም ደብዳቤው ለሱ ብቻ እንደተላከና የድርጅቱ አመራሮች ጭምር እንደማያውቁት አስረድቷል።የድርጅት አመራር ያላወቀውን ለምን የውጭ የድጋፍ አስተባባሪው እንዲያውቅ ተደረገ የሚል ጥያቄ ቢኖረንም አቶ እስክንድር ይህንን ለማድረግ የተገደደበት ሁኔታ ቢኖርበት ነው ብለን ወስደነዋል።በእኛም በኩል ያለው ግምት የአቶ እስክንድርን ጥንካሬና የትግል መንፈስ ስናሰላው ለመንግሥት ተንበርክኮ ከትግሉ ያፈገፍጋል አንልም።ዱሮም ቢሆን የኦሮሙማው ተረኛ ቡድን ለኢትዮጵያ ለሚጨነቁ የፖለቲካ ድርጅት መሪዎችና አባላት የሚራራ ልብ አለው ተብሎ አይጠበቅም። ስለሆነም እስክንድርና ሌሎቹ ችግር አይገጥመንም ብለው ትግሉን አልጀመሩትም፣ብዙ ችግሮችን እንዳሳለፉት ሁሉ ሌላውንም ተጋፍጠው ለማሳለፍ ወይም በሌላ የትግል መስክ ይሰለፋሉ እንላለን እንጂ እንደተራ ታጋይ ሁሉንም ነገር እምቦጭ አድርገውት ይሸሻሉ አንልም። ጸረ ኢትዮጵያ የሆነው የኦሮሙማው ቡድን አቶ እስክንድር ከፖለቲካ ሜዳ እርቆ በቤቱ ቢቀመጥም ሆነ ገዳም ቢገባ ተከታትሎ ያጠፋዋል እንጂ ይራራለታል አንልም።ምክንያቱም የጎን ውጋት የሆነበትን ድርጅት

ባልደራስን ፈጥሮበታልና ነው። ሁኔታውን የድርጅቱ የውጭ ግንኙነት ሃላፊ ነኝ ያሉት አንድ ዶር ሲገልጹ በድርጅቱ ውስጥ ምንም ችግር እንደሌለ፣እስክንድር እንደማንኛውም ግለሰብ የራሱን ውሳኔ መውሰድ መብቱ እንደሆነና በመልካም ሁኔታ ላይ እንዳለ፣ድርጅቱ ጠንካራ ተቋም በመሆኑ በቀላሉ ሊፈርስ እንደማይችልና ከግለሰቦች በላይ እንደሆነ፣ለውጩ የድጋፍ ኮሚቴም የተላከው ደብዳቤ በሁሉም ዘንድ የሚታወቅ እንደሆነ ማብራሪያ ሰጥቶ ነበር ።ይህ በእንዲህ እያለ ከአንድ ቀን በፊት ወ/ሮ አስካለ ደምሌ የተባለችው የድርጅቱ አመራር ስለተከሰተው ቀውስ ስትናገር፣ባልታሰበና ባልተጠበቀ መንገድ ስብሰባ ተጠራ፣እኔም በቢሮዬ እንዳልገባ ቁልፍ ተቀይሮ ጠበቀኝ፣እስክንድር በስብሰባው ላይ ባለመኖሩ ዬት አለ ብዬ ብጠይቅ አንድ ጊዜ በኮቪድ በሽታ ተገልሏል በሌላ ጊዜ ገዳም ገብቷል የሚል የተሳሳተ መረጃ ተሰጠኝ፣የፈለጉትን ተነጋገሩ፣እስክንድርን ለማግኘት ብሞክር አልተሳካልኝም ብላለች ሙሉ የድምጽ መልእክቷ የሚከተለውን ይመስላል።

https://youtu.be/lNsxtvAscfA

የኢትዮጵያን የፖለቲካ ድርጅቶች ታሪክ ስናጤን ከሚቃወሙት ሃይል በኩል ሊደርስባቸው ከሚችለው ጥቃትና ጉዳት በበለጠ ደረጃ የሚፈታተናቸው ብሎም ለመጥፋታቸው ምክንያት የሚሆነው ችግር በውስጡ ባሉት አባሎቹ መካከል በሚነሳ የሃሳብ ልዩነት፣ድክመት፣ክህደትና የዓላማ ጽናት አለመኖር እንደሆነ ብዙ ተመክሮዎችን ቀስመናል።በባልደራስ ውስጥም ተመሳሳይ ችግር ቢፈጠር አያስደንቅም።ሌላው ጉዳይ የፖለቲካ ድርጅት በአንድ ግለሰብ ትከሻ ላይ ከወደቀ ግለሰቡ ለሚደርስበት የጤና፣የአካልም ሆነ የፖለቲካ መስመር ለውጥ የተነሳ በድርጅቱ ላይ ሊጠገን የማይችል ስብራትና ለሌላው ታጋይ የተስፋ መቁረጥ ደረጃ ላይ እንደሚጥል መታወቅ አለበት።ይህንን አይነቱን አደጋ እንዳይከሰት ለማድረግ በብዙሃን ወይም በጋራ አመራር(collective leadership) የሚንቀሳቀስ መዋቅር ያለው ድርጅት መኖሩ ለስኬት ይበቃል። ግለሰብ ጋር ተያይዞ እንደ ዶሚኖ ወይም እንደ እምቧይ ካብ አይፈራርስም።ባልደራስ በዚህ አይነቱ ድክመት ውስጥ ተዘፍቋል የሚል ሽታ ቢሸተንም በአድርባይዎች እንዳይጠለፍና ከመፈራረስ ደረጃ ላይ እንዳይደርስ የድርጅቱ አመራርና አባላት ሊጠነቀቁ ይገባል። ተከስቶም ከሆነ ለደጋፊዎቹ ተገልጾ በመፍትሔ ፍለጋው እርብርቦሽ እንዲያደርጉበት ዕድሉን መስጠት ተገቢ ነው እንላለን።ባልደራስ ተዳከመ ወይም ተበተነ ማለት የአዲስ አበባ ሕዝብ ለመብቱ ተከራካሪውና ጠበቃውን አጣ ማለት ነው።እንደሌሎቹ ድርጅቶች ባልደራስ በአድርባዮችና ሰርጎ ገቦች ላለመዋጡ ዋስትና የለም። ባንዳና ለገንዘብ ያደረ ከሃዲ እስካለ ድረስ ብልጽግና ሰርጎ አይገባም ማለት አይቻልም።ለሁሉም እያደር ግልጽ እዬሆነ ይመጣል ብለን ተስፋ እናደርጋለን።

የባልደራስ አለመኖር ማለት አዲስ አበባም የትግል ሎኮሞቲቭ የመሆን ጉልበቷን ተነጠቀች ማለት ነው። ሎኮሞቲቭ ስንል እረጅሙን የባቡር ፉርጎ እዬጎተተ ከመድረሻው ቦታ የሚያደርሰው የሞተር ክፍልን አዲስ አበባ ካላት የፖለቲካ፣የኤኮኖሚና የማህበረሰብ ማእከልነት አኳያ በማነጻጸር ነው።አዲስ አበባ ሎኮሞቲቭ በመሆን ፉርጎ የሆኑትን ሌሎቹን ከተማዎች የማንቀሳቀስ ጉልበት አላት ማለታችን ነው። ሎኮሞቲቩም ካለፉርጎው ብቻውን እዬጮኸ ቢሄድ የባቡርነት አገልግሎቱን ተወጣ ማለት አይደለም ፤ ባቡርም አይባልም።ፉርጎውም ብቻውን ተቆርጦ ተገትሮ ከቀረ መጫኛ እንጂ የባቡር ፉርጎ አይባልም። ባቡር የሚባለው ሎኮሞቲቩና ፉርጎው ተሳስረውና ተያይዘው ሲጓዙና የያዙትን ጭነት ከታሰበው ቦታ ሲያደርሱት ነው።

አዲስ አበባ የተጀመረ ነገር ወደሌላው ክፍለሃገር በቀላሉ የመሻገሩን አቅም በተለያዩ የለውጥ ሂደቶች የታዘብነው ነው፤የመንግሥት መቀመጫ በመሆንም መናገሻ ከተማዎች ለስርዓት ለውጥ ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ።በአገራችን ዘውዳዊ ሥርዓቱን ያናጋው የዬካቲቱ 66 ከፍተኛው ሕዝባዊ እንቅስቃሴ የተካሄደው በአዲስ አበባ ከተማ ነው። ከዚያም ወዲህ የቱኒዚያው፣የካይሮው፣የሊቢያው፣የሱዳኑ--ወዘተ

መንግሥታዊ ለውጦች የመጡት በመናገሻ ከተማዎች በተጀመረ ሕዝባዊ አመጾች ነው።አሁንም የአዲስ አበባ ነዋሪ የለውጡ መንኮራኩር ወይም ሎኮሞቲቭ ነው እንላለን።ለዚያም ነው የኦሮሙማው አጥፊ ቡድን በአዲስ አበባ ላይ ሙጭጭ ብሎ ዓይን ባወጣ ዘረፋ ላይ የተሰማራው፤ሕዝቡንም የቁም ስቃዩን የሚያሳዬው፣ስለሱም የሚከራከረውን ባልደራስን ለማጥፋት ያለ የሌለ ሃይሉን ያሰለፈው።

የባልደራስ ለእውነተኛ ዴሞክራሲ አመራሮች በነሓሴ 22 ቀን ጠቅላላ ስብሰባ መጥራታቸውን ሰምተናል። ሌላ ተተኪ የፓርቲው መሪ (መሪዎች) ለመምረጥና ድርጅቱን አገራዊ ፓርቲ ለማድረግ እንደሆነ ገልጸዋል።የመጣባቸውን አደጋ ተቋቁመው የሚያሶግዱበትና በጥንካሬ የሚወጡበት የተሳካ ጉባኤ እንዲሆንላቸው ከልብ እንመኛለን!

የአዲስ አበባ ነዋሪም ሆነ ሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደ ሕዝብ ተከብሮ የአገር ባለቤት ሆኖ መኖር የሚችለው ለያይቶ ሊያጠቃው የመጣውን የጎሰኞች ስርዓት ለመጣል ተባብሮ ሲነሳ ብቻ ነው። በመታገል ያለበትን የስቃይ ኑሮና የታሰረበትን የባርነት ሰንሰለት እንጂ የሚያጣው ነገር የለም። የሚያተርፈው ቢኖር ሰብአዊ ክብሩንና የአገር ባለቤትነቱን ነው።

ሌላው የዘገባ ትኩረታችን ከወር ወዲህ እዬጠነከረ የመጣው የጉራጌ ማህበረሰብ ተወላጆች ክልል የመሆን ጥያቄ የሚመለከት ይሆናል።ደግመን ደጋግመን እንደገለጽነው ክልል የሚለውን አገራዊ አወቃቀር የምንቃወመው ነው።ለምን ዓላማ እንደተፈጠረ ስለምናውቅ ለክልል ስስ አንጀት የለንም። ወያኔና መሰሎቹ ኢትዮጵያን ለመበታተን የሕዝቡን ታሪካዊ ትስስር ለመበጠስ ያቀዱት የከፋፍለህ አጥፋ ስልት በመሆኑ እኛ ብቻ ሳንሆን ሌላው አገር ወዳድ፣ስለሰው ልጆች እኩልነትና የጋራ ሙብት የሚጨነቁ ፣በመንገዱ አልፈው መከራውን የቀመሱ ሁሉ የሚያወግዙት እኩይ ድርጊት ነው።ለጉራጌም ሆነ ለሌላው ወገናችን ለመግለጽ የምንወደው ክልል መሆን የሕዝቡን የመከራ ኑሮ የሚያሶግድ እንዳልሆነና የራሱን ቋንቋ በሚናገሩ የራሱ ጎሳ ተወላጆች የሚጨቆንበትንና የሚዘረፍበትን መንገድ መምረጥ እንደሆነ ነው።በክልል አወቃቀር አገሩን ኢትዮጵያን ለማጥፋት የተነሱትን ደግፎ መሰለፍ ማለት እንደሆነ ሊያውቀው ይገባል እንላለን።በክልል ቀደም ሲል የተከለሉት ዜጎች ኑሯቸው አልተቀዬረም።በፈለጉበት ቦታ ሄደው የመሥራትና የመኖር መብታቸውን ተገፈው በጠባብ መሬት ውስጥ የታሠሩ እሥረኞች መሆናቸውን ለማወቅ እሩቅ መሄድና መመራመር አያስፈልግም፣በአገራችን ውስጥ የሚካሄደውን ማዬቱ በቂ ነው።

ከጉራጌው ማህበረሰብ ትግል ሌላው ሊማር የሚገባው ነገር ቢኖር ክልል ለመሆን ተባብረው መነሳታቸውና በአጭር ጊዜ ውስጥ የፈለጉትን ለማግኘት ግማሽ መንገድ ላይ ለመድረስ የበቁበትን አንድነታቸውን አለማድነቅ ክህደት ይሆናል።ብልጽግና ከተባለው ምስለኔዎች የከባቢ ባለሥልጣናት ጀምሮ የአገር ሽማግሌዎች የተካተቱበት ይህ ጥያቄ መንግሥት ነኝ ባዩ ቡድን ያሰበውን ለመጫን የማይችልበት ሕዝበ ውሳኔ ላይ መድረሱ ለሌላው ማህበረሰብ በዓላማ ጽናትና በአንድነት መቆሙ ለሚፈልጉት ድል ሙብቃት እንደሚያስችል የሰጠው ትምህርት የሚደነቅ ነው።ያልታደለው አማራ በቁጥርም በስቃዩም መጠን ከሌሎቹ ግዙፍ ቢሆንም፣ላለፉት 32 ዓመቶች የራሱ ክልል ኖሮት መሪዎች አሉት ቢባልም፣ ከሚደርስበት ስቃይና መከራ፣መጨፍጨፍና መፈናቀል ሊድን አልቻለም።ያም የሆነው እንደ ጉራጌ ወገኖቹ የዓላማ ጽናት ያለው አንድነት ባለመኖሩና ለጥቃት በመጋለጡ ነው። በስሙ ሥልጣን ላይ የወጡት የክልሉ ምስለኔዎች ለህሊናቸው ያላደሩ፣በገዛ ጎሳቸው ላይ የሚዘምቱ የአገር አጥፊው ቡድን የኦሮሙማው ብልጽግና ከዚያም በፊት የወያኔ መራሹ ኢሕአዴግ አካልና ተላላኪ በመሆናቸው ነው።እንደ አማራው የጥቃት ብዛትና ሰቆቃ፣እንደ ብዛቱ ቢሆንማ ኖሮ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በሌላው የአፍሪካ አገሮች ተከብሮና ተወዶ መኖር በቻለ ነበር።ለዚያ መታደል ሳይሆን ተሰዶ

ለመኖር እንኳን አልቻለም።በተለያዩ አገሮች እሥር ቤት ይማቅቃል፤ባሕር አቋርጦ ለመሰደድም ቢሞክር በመርከብ ወይም ጀልባ ላይ በደረሰ አደጋ የአሳ ነባሪ ቀለብ የሆነው ብዙ ነው።

ተወደደም ተጠላም እንደ ጉራጌ ወገኖቹ ለሚፈልገው ዓላማ በአንድነት መቆም ይኖርበታል።የጉራጌ ተወላጅ ወገኖቻችንን ለማሳሰብ የምንወደው ለትንሽ ክልል ያደረጋችሁትን ትግልና አንድነት ለታላቋ አገራችሁ ለኢትዮጵያ አንድነትና ልዑላዊነት እንድታደርጉት ነው።እንደሚያደርጉትም እንተማመናለን።

ከሰሞኑ ያገራችን ከፍተኛ ክንውኖች አንዱ የአባይ የሦስተኛው ሙሌት በመጠናቀቅ ላይ መሆኑና የሁለተኛው ጄኔሬተር ሃይል ማመንጨት መጀመሩን የሚያሳዬው መልካም ውጤት ነው።በአባይ ግድብ ላይ ጠላት ካልሆነ የሚከፋው አገር ወዳድ የለም።መገደቡን እንደግፋለን።ከመገደቡ ጋር ተያይዞ ግን እውነት ለሕዝቡ ጥቅም ይውላል የሚል ጥያቄ ማንሳቱም ተገቢና አስፈላጊ ነው።ይህ በዛሬው ሙሊት ሥራውን ጀመረ የተባለው ጄኔሬተር ቀደም ሲል እንደተተከለና ሃይል ማመንጨት እንደጀመረ መገለጹን እናስታውሳለን።ከወራት በኋላ ግን አንዱ ብቻ ሃይል ማመንጨቱ ይፋ ሆኗል።

ኢትዮጵያ ከአባይ ግድብ ውጭ በሌሎቹ ግድቦች በምታመርተው 3820ሜጋዋት የኤሌክትሪክ ሃይል ከአፍሪካ የመጀመሪያውን ቦታ የያዘች አገር ናት።ግን ለሕዝቧ በማቅረብ ደረጃ በሁለተኛ ደረጃ ካለችው ባለ3595 ሜጋዋት ደቡብ አፍሪካ፣ከሶስተኛዋ የ3083 ሜጋዋት ባለቤት ከሆነችው አንጎላ፣ በ ከአራተኛ ደረጃ የ2886 ሜጋዋት ባለቤት ከሆነችው ከኢጅብት ቀርቶ በአስረኛ ደረጃ የ1770 ሜጋዋት ባለቤት ከሆነችው ሞሮኮ ያነሰ ነው።አሁንም ቢሆን በአባይ ግድብ ላይ የታሰበው የ13 ጀኔሬተር ሥራ ቢጠናቀቅ በጭስና በጨለማ ለሚበሳቆለው ገጠሬ ኢትዮጵያዊ ይተርፈዋል የሚል እምነት የለንም። የስካሁኖቹም ሆኑ የአባይ ሃይል ለሽያጭ የሚቀርብ ሸቀጥ ከመሆን ያለፈ ሙሉ ለሙሉ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያገለግላል አንልም።ይህንንም ስንል በጭፍን ተነስተን አይደለም።በቅርቡ የኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ ኮርፖሬሽን ባወጣው መግለጭ ለጎረቤት አገር በተሸጠ የኤሌክትሪክ ሽያጭ በ6 ወር ውስጥ ከ90 ሚሊዮን ዶላር በላይ ማግኘቱን ይፋ አድርጓል።ገንዘቡ ግን ለምንና በምን ላይ እንደዋለ የሚያውቁት ሻጮቹና ባለሥልጣኖቹ ናቸው።ከሁሉም በላይ ግን አገሪቱ ከተዘፈቀችበት የጎሳ ፖለቲካና የክልል ስርዓት ካልወጣች አባይም ሆነ ሌሎቹ ግድቦች የኢትዮጵያ ሕዝብ ንብረትነታቸው ከጥርጣሬ ያለፈ ይሆናል። በሙብራት ሃይል ዙሪያ በሰሞኑ የተሰማው ዜና በምሥራቅ አፍሪካ አካባቢ ኢትዮጵያን፣ ኤርትራን፣ጅቡቲን፣ደቡብ ሱዳንን፣ኬንያን፣ኡጋንዳን ፣ ጨምሮ በዓለም ባንክ፣በአይኤም ኤፍ(IMF)፣ በአሜሪካ መንግሥና በፈረንሳይ መንግሥት ሽርክና የኤሌክትሪክ ሃይል የማመንጨት ውል እንደተፈረመ ለማወቅ ችለናል።ይህ ውል በሥራ ላይ ያሉትንና በግንባታ ላይ ያለውን የህዳሴ ግድብ ማጠቃለል አለማጠቃለሉን የሚያስረዳ ዝርዝር አላገኘንም። አባይ ተሸጧል የሚባለውም ከግምት ውስጥ እንዲገባ የሚያደርገው የዚህ አይነቱ እንቅስቃሴና ጥምረት ነው።እሳት በሌለበት ጭስ አይጨስም ይባላልና አይሆንም አይባልም።ተደብቆ የሚቀር ነገር የለም፤ ሁሉንም ጊዜ መስተዋቱ ያሳዩናል።

አባይ ተሽጧል የሚለውን ከሚያጠናክሩት ውስጥ ጠቅላላ ግንባታውን ለመጨረስ 80 ቢሊዮን የኢትዮጵያ ብር (5 ቢሊዮን ዶላር)ይፈጃል የተባለው ገና ሥራው ሳይጠናቀቅ ገና 70% ላይ እያለ 121 ቢሊዮን የኢትዮጵያ ብር መፍጀቱን ሰምተናል።ከዚያም ውስጥ ከኢትዮጵያ ሕዝብ የተሰበሰበው ገንዘብ መጠን 11 ቢሊዮን የኢትዮጵያ ብር ነው ተብሏል፤ታዲያ ቀሪው 110 ቢሊዮን የኢትዮጵያ ብር ከዬት መጣ?ይህም ገንዘብ ባሁኑ ደረጃ ሥራ ላይ የዋለውን እንጂ የወደፊቱን 20% ሥራ የሚጨምር አይደለም።በቀጣይ ብዙ ቢሊዮን ብር ያስፈልጋል ማለት ነው።ከዬት ይመጣል?

በአጃንስ ፍራስ ፕሬስ በኩል ተገኘ ብለው ሌሎቹ ያገር ውስጥ ወሬ አቀባዮች እንደገለጹት ከሆነ የወያኔና የኦሕዴድ /ብልጽግና ተወካዮች ውይይት መጀመራቸውን የአፍሪካ ህብረት በድረገጹ ላይ ማስፈሩን ዋቢ በማድረግ መጥቀሳቸውን ሰምተናል።የሁለቱ መደራደርና መስማማት አገሪቱን ተባብረው በማፍረሱ ላይ እንጂ የተለዬና የተሻለ ሁኔታ ይፈጥራሉ ተብሎ አይጠበቅም።እንሱ ተስማሙም ተጣሉም እዳው የሚተርፈው ለሕዝቡ ነው።ስለሆነም ከነሱ ቀድሞ መወያዬትና መስማማት ብሎም መደራጀት ያለበት ሕዝቡ ነው እንላለን።ያልተደራጀ ተፈጀ!

የሽግግር መንግሥት ይቋቋም፣የጎሰኞች ስርዓት ይወገድ!!

ኢትዮጵያ በአንድነትና በነጻነት ለዘላለም ትኑር!